# የፌደራል ማገገሚያ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ረቂቅ መመሪያ ቁጥር

# 240/2013

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

ነሐሴ 2009 ዓ.ም

# የፌደራል መንግሥት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ረቂቅ መመሪያ ቁጥር240/2013

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አወጣጭ ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ''የፌደራል መንግሥት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መመሪያ ቁጥር 240/2013'' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ ያሉ ቃላትና ሃረጎች በፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለው) እና በፌደራል መንግስት የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ ወስጥ፡-

1. **"የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት"** ማለት የመንግሥት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠየቂነት ሚጃዎችን ለህብረተሰቡ ለማድረስ እና ህብረተሰቡን ለማሳተፍ የሚከናወኑ ሥራዎችን ለማከታተል እንዲሁም ለተገኙ አሉታዊ ወጤቶች ወይም ላልተፈፀሙ ሥራዎች ተጠየቂነትን ለሚያጋገጥ የተዘረጋ ሥርዓት ነው፡፡

2. **"የመንግስት ፋይናንስ** ግልጽነትና ተጠየቂነት **መረጃ"** ማለት ለዜጎች የሚቀርብ ወቅታዊ እና ተከታታይነት ያለው የመንግስት በጀት፣ የማስረታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ፣ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም፣ የመንግስት ግዥ አፈጻጸም እና የኦዲት ግኝት ሚጃዎች ናቸው፡፡

3. **."የመሠረታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ" ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከመንግሥት በተመደበ በጀት ወይም ከመ/ቤቱ የውስጥ ገቢ ከተገኘ ገንዘብ ወይም ከልማት አጋሮች ከተገኘ ብድርና እርዳታ ለሁሉም ዜጎች ወይም ለተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል የሚሰጥ የትምህርትና ስልጠና፣ የጤና ክብካቤ፣ የውሃና አካባቢ ጽዳት፣ የግብርና፣ የመንገድ ግንባታና የሌሎች አገልግሎቶች አሰጣጥ ደረጃ መረጃ ማለት ነው፡፡**
4. **"አመላካች/ቴምፕሌት"** ማለት የመንግሥት በጀት (ገቢና ወጪ)፤ የማሰረታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ፣ የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ደረጃ፣ የመንግስት ግዥ አፈጻጸም ሂደት እና የኦዲት ግኝት መረጃዎችን በሠንጠረዥ ወይም ሌሎች ልዩ ልዩ የማቅረቢያ ዘዴዎችን በማጠቃም ለህብረተሰቡ የሚደርስበት መዛሪያ ወይም ስልት ነው፡፡

## 4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001(እንደተሸሻለው) የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ተብለዉ በተመለከቱት ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 5. <u>ዓላማዎች</u>

የዚህ መመሪያ ዓላማዎች፡-

1. የመንግስት መ/ቤቶች የመንግሥት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መረጃዎችን በተዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሠረት ዜጎች በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉበት ዘዴ በወቅቱና በተሟላ መልኩ ተደራሽ እንዲያደርጉ በማድረግ ግልጽነትና እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣

2. የዜጎች ተሳትፎን በማጐልበት ወጤታማነት እና የህዝብ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልካም አስተዳደርን ማስፈን፣

ናቸው፡፡

## 6. <u>መርሆዎች</u>

የመንግስት መ/ቤቶች ማንኛውንም የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ተግባር ሲያከናውኑ የሚከተሉትን መርሆች መሰረት ማድረግ አለባቸው፡-

1. የመንግስት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት መረጃዎች ህብረተሰቡ ሊረዳው በሚችል መልኩ ተሟልቶ እና ወቅቱን ጠብቆ ተደራሽ መደረጋቸውን፣

2. የዜጎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለሚረጋገጥ የፕሮግራሙ ወይም የፕሮጀክቱ ወይም የተግባሩ ቀጥታ ተጠቃሚ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል በበጀት ሂደቱ በተሟላ ሜኩ የሚሳተፍበት ምቹ ሁኔታ የተፈጠረለት መሆኑን፣

3. በማንኛውም የበጀት ምንጭ የሚከናወኑ ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች ወይም ተግባራት በዕቅዱ መሠረት በቁጠብ፣ በብቃት፣ በጥራት እና በውጤታማነት የተከናወኑ እንዲሁም በአፈፃፀም የሚታዩ አሉታዊ ልዩነቶች ተጠያቂነት የሚያስከትሉ መሆኑን፣

# ክፍል ሁለት

## ተግባርና ኃላፊነት

### 7. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

ሚኒስቴሩ፡ –

1. መሠረታዊ የፌደራል መንግሥት የበጀት ሚጃዎችን እና ሌሎች የመንግሥት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ሚጃዎችን በድረ – ገጹ እና በሌሎች ተደራሽ በሆኑ የመገናኛ ብዙኃን ዘደዎች አማካኝነት ለህብረተሰቡ እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርጋል፣
2. የመንግስት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት፣ በበጀት ዓመቱ ወስጥ ከልዩ ልዩ ምንጮች በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ያገኙትን የዕርዳታና የብድር ገንዘብ ሚጃ በግልጽ ለህብረተሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ሚድረጋቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣
3. የመንግስት መ/ቤቶች በአገር ደረጃ ከተቀማጠው የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ግብ አኳያ ባለፈው በጀት ዓመት የተደረሰበት እና በበጀት ዓመቱ ሊደረስበት የታቀደውን የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ሚጃ በግልጽ ለህብረተሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ሚድረጋቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣
4. የመንግስት መ/ቤቶች የመንግሥት ግዥ አፈጻጸም ሂደት እና የኦዲት ግኝት ሚጃዎችን ለህብረተሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ሚድረጋቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣
5. ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ይቀበላል፣ ይገመግማል፣ ሪፖርቱን በማጠቃለል ሚጃውን ለዜጎች እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርጋል፣

6. በማግሥት ሙሥሪያ ቤቶች በተጨዋኒት የሚቀረቡ አዳዲስ የሚጃ ማስረጫ ስልቶች/ዘዴዎች ካሉ በማምገም ሥሩ ላይ እንዲውሉ ይፈቅዳል፣
7. ለአስፈፃሚ አካላት፣ ለዜጎችና ባለድርሻ አካላት እንደአስፈላጊነቱ የግንዛቤ ማስጨጫ ሙድረኮችን በማዘጋጀት ሥልጠና ይሰጣል፡፡

## 8. <u>የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት</u>

**የመንግስት መ/ቤቶች፡ -**

1. ለመደበኛ ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት ወይም ተግባራት ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን በጀት፣ በበጀት ዓመቱ ወስጥ ከልዩ ልዩ ምንጮች በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ያገኙትን የዕርዳታና የብድር ገንዘብ ወቅታዊ እና የተሟላ ሚጃ ቀላልና ግልጽ በሆነ መንገድ ለህብረተሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርጋሉ፣
2. በአገር ደረጃ ከተቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ግብ አኳያ ባለፈው በጀት ዓመት የተደረሰበትን እና በበጀት ዓመቱ ሊደረስበት የታቀደውን የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ሚጃ ቀላልና ግልጽ በሆነ መንገድ ለህብረተሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርጋሉ፣
3. የመ/ቤቱን የግዥ አፈጻጸም ሂደት እና የኦዲት ግኝት ወቅታዊ እና የተሟላ ሚጃዎችን ቀላልና ግልጽ በሆነ መንገድ ለህብረተሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርጋሉ፣
4. የየሩብ ዓመቱን የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ሩብ ዓመቱ ባለቀ በ15 ቀናት ወስጥ ለሚኒስትሩ ያቀርባሉ፣
5. በህግ ከተሰጣቸው ኃላፊነትና ተግባር አንፃር ለዜጎች ወይም ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ተደራሽ መሆን አለባቸው በማለት ከዚህ መሙሪያ ጋር አባሪ ተደርገው ከተላኩት አማካኞች/ቴምፕሌቶች በተጨማሪ የሚቀርፁዋቸው አዳዲስ የሚጃ ማስረጫ ስልቶች ካሉ ለሚኒስቴሩ አቅርቦ በማስፈቀድ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፡፡

# <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ለዜጎች እና ለባለድርሻ አካላት የሚገለፁ ሚጃዎች</u>

## 9. <u>በሚኒስቴሩ የሚገለፁ መረጃዎች</u>

***ሚኒስቴሩ ከዚህ በታች የተመለከቱትን መሰረታዊ የበጀት እና የኦዲት*** የመንግሥት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ***መረጃዎችን በተዘረጋው የአሠራር ሥርዓት*** ማስረት

**በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለዜጐች እና ለባለድርሻ አካላት ግልጽ ማድረግ አለበት ፡-**

1. የአስፈጻሚ አካላት የበጀት ዕቅድ አጠቃላይ መዝገኛ የሆኑትን ወጪ፣ የገቢ ዕቅድን፣ እና የዕዳ ማጠንን የሚማከቱ ሚጃ መግለጫዎችን (**የቅድመ በጀት መግለጫ**) ቢያንስ የበጀት ዓመቱ ከመጀመሩ አራት ወራት በፊት፣

2. ጥቅል የአስፈጻሚ አካላት ዓመታዊ የበጀት ዕቅድ ሰነድን ለህግ አወጪው በቀረበ በአንድ ሳምንት ጊዜ ወስጥ፣

3. በህግ አወጪው ህግ ሆኖ የፀደቀወን የዓመቱን በጀት በፀደቀ በሁለት ሳምንት ጊዜ ወስጥ፣

4. ግልጽና ቀላል ማጠቃለያ የአስፈጻሚ አካላት የበጀት ዕቅድን እና የፀደቀ በጀትን (የዜጎች በጀት) እንደአስፈላጊነቱ በአካባቢያዊ ቋንቋ ተተርጉሞ እንደቅደምተከተላቸው ለህግ አውጭው በቀረበ በሁለት ወራት ጊዜ ወስጥ እና በጀቱ በፀደቀ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ፣

5. የወር ወይም የሩብ ዓመት የበጀት አፈጻጸም ሪፖርትን ሪፖርቱ በወጣ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ፣

6. በበጀት ዓመቱ አጋማሽ አጠቃላይ በጀቱ ያስገኘው ወጤት ላይ የተደረገ ወይይትን እና በፀደቀው በጀት ፖሊሲ ላይ ተጽዕኖ በማሳደራቸው የተሻሻሉ ኢኮኖሚያዊ ታሳቢዎች ካሉ ግማሽ ዓመቱ በተጠናቀቀ በሁለት ወራት ጊዜ ወስጥ፣

7. ዓመታዊ የበጀት አጠቃቀም ሪፖርትን የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በስድስት ወራት ጊዜ ወስጥ፣

8. የወጪ ኦዲት ሪፖርትን ያካተተ ዓመታዊ የፋይናንስ ኦዲት ሪፖርትን የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ12 ወራት ጊዜ ወስጥ (ቀጣዩ በጀት ዓመት ከማጠናቀቁ በፊት)፣

## 10. በመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሚገለጹ መረጃዎች

### 1. በመደበኛነት የሚገለጹ የአገልግሎት አሰጣጥ መረጃዎች

የመንግስት መ/ቤቶች ከዚህ በታች የተመለከቱትን በመደበኛነት የሚገለጹ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የመንግሥት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት **መረጃዎችን ለዜጐች እና ለባለድርሻ አካላት ግልጽ ማድረግ አለባቸው፡-**

ሀ. የሙሂያ ቤቱን ስም ፤ራዕይ ፤ተልዕኮና እሴቶች፣

ለ. የመንግሥት ሙሂያ ቤቱን የበላይ ኃላፊ የቢሮና የስልክ አድራሻ፣

ሐ. የበጀትና ወጪ አፈጻጸም ሚጃዎችን ከዚህ መሜያ ጋር በተያያዘው ዕዝል 1 ማሰረት፣

መ. ዋና ዋና የማሰረታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ሚጃዎችን (በማሰረታዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት) ከዚህ መሜያ ጋር በተያያዘው ዕዝል 2 ማሰረት፣

ሠ. የኦዲት ግኝት እና የሚስተካከያ እርምጃ ሚጃዎችን ከዚህ መሜያ ጋር በተያያዘው ዕዝል 3 ማሰረት፣

ረ. በየዘርፉና በየመ/ቤቱ የሚከራ(ሩ) ትላልቅ ፕሮጀክቶች ዕቅድን፣ የበጀትና የአፈጻጸም ሚጃዎችን ከዚህ መሜያ ጋር በተያያዘው ዕዝል 4 ማሰረት ፤

ሰ. የመንግሥት የግዥ ዕቅድና የግዥ አፈፃፀም ሂደት ሚጃዎችን ከዚህ መሜያ ጋር በተያያዘው ዕዝል -------- ማሰረት

## 2. የዕርዳታ እና ብድር ሚጃዎች፡ -

**የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከማዕከላዊ መንግሥት ግምጃ ቤት ከተመደበላቸው በጀት በተጨማሪ ለተለያዩ ፕሮግራሞች ወይም ፕሮጀክቶች ወይም ተግባራት ማስፈፀሚያ ከተለያዩ ምንጮች በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት ያገኙትን የዕርዳታና የብድር ገንዘብ በተመለከተ የሚከተሉትን መረጃዎች** ለዜጎች ግልጽ ሚድረግ አለባቸው፡ -

**ሀ. በዕርዳታና በብድር የተገኘውን** የገንዘብ ማጠን፣

ለ. በፕሮግራሙ ወይም በፕሮጀክቱ ወይም በተግባሩ ሊሳካ የታሰበው ዓላማ ፤

ሐ. በፕሮግራሙ ወይም በፕሮጀክቱ ወይም በተግባሩ ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሚሆነው የማህበረሰብ ክፍል፤

መ. የፕሮግራሙ ወይም የፕሮጀክቱ ወይም የተግባሩ ተጠቃሚዎች የተለዩበት ማስፈርት፣

ሠ. በፕሮግራሙ ወይም በፕሮጀክቱ ወይም በተግባሩ የተገኘ ጥቅም እና የተሳካ ወጤት፣

3. የመንግስት መ/ቤቶች ለህዝብ ይፋ የሚያደርጉትን የመንግሥት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ሚጃዎችን እንደየዓይነታቸውና ይዘታቸው የተዘጋጀላቸውን ቅጾች (ከዚህ መሜያ ጋር ተያይዞ በቀረበው ዕዝል እንደተማለከተው) እንዲሁም የመንግሥት ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማትን በማጠቀም ሞልተው በማዘጋጀት በሙሂያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከተፈረመ በኋላ የሙሂያ ቤቱ ማህተም ተደርጎበት አመቺ በሆኑ የሚጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎች አማካኝነት ለዜጎች ግልጽ ሚድረግ አለባቸው፡፡

# 11. የመረጃ ማስተለለፊያ ዘዴዎች

የማንግስት ማሥሂያ ቤቶች ከሚሰጡት አገልግሎት ባህሪ አንፃር እየማዘኑ ከሚከተሉት የሚጃ ማስተላለፊያ ዘደዎች ቢያንስ 3ቱን በማጠቀም የማንግሥት ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠየቂነት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ሚጃዎችን ተደራሽ ሚድረግ አለባቸው፡ –

ሀ.በማሥሂያ ቤቱ ድረ–ገጽ፣

1. ለ.በቴሌቭዥን፣

2. ሐ.በሬዲዮ፣

3. መ.በባነር፣

4. ሠ.በበራሪ ወረቀቶች (ብሮሸር)፤

5. ረ.በህትመት ወጤቶች (ሚጽሄቶች እና ጋዜጦች)፣

6. ሰ.በማህበራዊ ሚዲያ ( ፊስቡክ፤ቲዊተር ወዘተ…)

7. ሸ.በቲቪ ስክሪን፣

8. ቀ. በማስታወቂያ ማለጠፊያ ሰሌዳዎች፡፡

## 12. <u>የሚጃ ማስተላለፊያ ጊዜ ሰሌዳ፤</u>

የማንግሥት ማሥሂያ ቤቶች ከዚህ በታች በተማለከተው የጊዜ ሰሌዳ ማስረት የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠየቂነት ሚጃዎችን ለዜጎች እና ለባለድርሻ አካላት ግልጽ ሚድረግ አለባቸው፡ –

1. የበጀትና የወጪ ሚጃዎችን በየሩብ ዓመቱ ሆኖ፡ –
   ሀ. የአንደኛ ሩብ ዓመት ሚጃዎችን እስከ ጥቅምት 15 ድረስ፣
   ለ. የሁለተኛ ሩብ ዓመት ሚጃዎችን እስከ ጥር 15 ድረስ፣
   ሐ. የሦስተኛ ሩብ ዓመት ሚጃዎችን እስከ ሚያዝያ 15 ድረስ፣
   መ. የአራተኛ ሩብ ዓመት ወይም ዓማታዊ የተጠቃለለ ሚጃዎችን እስከ ነሐሴ 15 ድረስ፣
2. የማሰረታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ሚጃዎችን በዓመት አንድ ጊዜ በሐምሌ ወር ሶስተኛ ሳምንት፣
3. የማንግሥት የግዥ ዕቅድና የግዥ አፈፃፀም ሂደት ሚጃዎችን በግዥ ሕጉ በተቀማጠው የጊዜ ገደብ ፣
4. የወጪ እና የወስጥ ኦዲት ዋና ዋና የኦዲት ግኝት ሚጃዎችን ግኝቶቹ ለሜጅማንት ቀርበው የማውጫ ስብሰባ በተደረገ በ15 ቀን ወስጥ፣
5. የካፒታል ፕሮጀክቶች የፊዚካልና የፋይናንሺያል ሚሃ ግብር ሚጃዎችን እስከ ሐምሌ 30 ድረስ፣

# <u>ክፍል አራት</u>

# <u>ልዩ ልዩ</u>

## 13. ከተባባሪ አካላት ጋር የሚደረግ ጥምረት

1. የማግሥት መ/ቤቶች የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ሲተገብሩ ከሌሎች የዜጎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ተግባሪ አካላት (የማህበራዊ ተጠያቂነት እና ቅሬታ ሰሚ አካላት) ጋር ጥምረት በመፍጠር የዜጎችን ተሳትፎ ማጎልበት አለባቸው፡፡
2. የማግሥት ማስሪያ ቤቶች ከተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት አንፃር በካፒታል ፕሮጀክቶች ዕቅድና በጀት አፈጻጸም ላይ በየሩብ አመቱ ሩብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ ከተጠቃሚው ህብረተሰብ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር መወያየት አለባቸው፡፡

## 14. አስተዳደራዊ እርምጃዎች፡ -

በፋይናንስ አስተዳደር ኃላፊነትን በአግባቡ ባለመወጣት የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች መመሪያ ቁጥር 48/2009 የተደነገጉት የቅጣት ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

# ክፍል አምስት

## 15. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ--------------------ቀን 2009 ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

---------------- ቀን 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አብራሃም ተከስተ (ዶ/ር)

የኢፌዴሪ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሚኒስትር